# ቤተ ክርስቲያን በገዛ ልጆችዋ ስትፈተን!

## ቁጥር ፫

በአለፈው በቁጥር ፪ ላይ ከምእመናን በየጊዜው ከቀረቡት ጥያቄዎች መካከል ፥የተወገዙ መምህራን ስብከት
ለምን በዚህ ዌብ ሳይት ላይ ይደመጣል ተብሎ ለተጠየቀው፤ አባ ወልደ ትንሣኤን አስመልክቶ መልስ
ሰጥተናል። በዛሬው ቁጥር 2 ጽሑፋችን ደግሞ ቀሲስ መላኩና እንዲሁም ሌሎችም ሰባክያን ቅስና ከመቀ
በላቸው በፊት በአንድ ወቅት ወደ ሌላ የእምነት ክፍል ገብተዋል ወይም የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ዓይነ
ት ባህርይ አሳይተዋል፤ ስለዚህ ተመልሰው ወደ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ቢመጡም የቅስና ማዕረግ
መቀበል የለባቸውም ወይም ደግሞ ቀኖናቸውን አልጨረሱምና የተወገዙ ናቸው እያሉ፤ በየክፍለ ዓለሙ በ
አሜሪካ፣ በጀርመን በሌሎችም ከተማዎች ምዕመናንን እየሰበሰቡ ግራ በማጋባት መምህራንን ተቀባይነት እ
ንዳይኖራቸው ለማድረግ «ማኅበረ ቅዱሳን» ከፍ ያለ ጥረት ስለማድረጉና በተጨማሪም በሀገር ቤት ያሉ
መምህራን ላይ ይኸው ማኅበር ስለሚያደርገው የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው።

በመሠረቱ ከእነዚህ መምህራን መካከል ሆነው የነበሩ ካሉ አስፈላጊው ቀኖና ተሰጥቷቸው ተመልሰው
የሚያገለግሉ ሲሆኑ፤ ሌሎች ደግሞ ገና ለገና ወደ ሌላ እምነት ሄደው ሊሆኑ ይችላሉ በሚል ጥርጣሬ ነው
ይህ የስም ማጥፋት ዘመቻ የሚካሄድባቸው። ሁላችንም ማወቅ ያለብን ግን ሥልጣነ ክህነቱን የሚሰጠው
አንድ ሊቀ ጳጳስ ብዙ ነገሮችን የማድረግ መብት እንዳለው በፍትሐ ነገሥቱ ተዘርዝሯል። ከነዚህም አንዱ
ለአንድ ሰው ሥልጣነ ክህነትን የመስጠት ነው። ሊቀ ጳጳሱም ሁሉንም ሁኔታ ካጣራ በኋላ ሰውየው የሚገ
ባው ሆኖ ካገኘው ይሾመዋል። አለ አግባብ ከሾመው ደግሞ፤ እንደ ሥልጣን ተዋረዱ ከላይ ይጠየቅበታል
እንጂ በጣም ከታች በሰንበት ት/ቤት መምሪያ ሥር ያለው «ማኅበረ ቅዱሳን» ሊቀ ጳጳሱ የሾመው አይሠ
ራም ብሎ በተናጥል በየክፍለ ዓለሙ እየዞረ የተሾመው ቄስ አይደለም ፓስተር በሉት እያለ አለ መብቱ
ገብቶ በስብከታቸው የስንት ሰው ሕይወትን በትምህርታቸው የሚማርኩ መምህራንን ስም ማጥፋት ክርስቲያ
ናዊ ምግባር አይደለም። «ማኅበረ ቅዱሳንን» ከላይ የተነገረው ውሳኔ ሰምቶ መፈጸም እንጂ፤ ቤተ ክርስቲ
ያንና ምዕመናንን የሚከፋፍል ሥራ መሥራት የቤተ ክርስቲያን አንድነትና ሰላምን የሚያናጋ ይሆናል።

ሊቀ ጳጳሱም የሚሾማቸውን ካህናት ሕይወታቸውን፣ የንስሐ ቀኖናቸውን ሌሎችንም የተያያዙ ነገሮችን ሲያጣራና ሲወስን «ማኅበረ ቅዱሳንን» እያማከረ አይደለም። ማኅበረ ቅዱሳን በወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ሥር የተቋቋመ ክፍል እንጂ በጳጳሳት/ሲኖዶስ ሥራ ክፍል ውስጥ እየገባ የሚፈነጭ አካል አይደለም። የሥልጣን ተዋረዱ መኖሩን መዘንጋት የለበትም። አለቦታቸው ገብተው መፈትፈት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። አንዳንዶቹም የስም ማጥፋት ዘመቻቸው ተቀባይነት እንዲኖረው በፍትሐ ነገሥት ላይ «ማንም ከእምነቱ ወጥቶ ወደ ሌላ ከሄደ ዳግም ቢመለስ አይሹም ይላል» በማለት ምእመናንን ያደናግራሉ። ይህ ደግሞ ፍጹም ሐሰት ነው። ይህን ፍትሐ ነገሥት የሚጠቅሱትም ብዙ ሰው አያገኘውም ወይም አያውቀው ም በማለት ነው። እናንተም አይታቸሁ እንዲህ ዓይነት መመሪያ በመጽሐፉ ላይ እንደሌለ እንድትረዱት በማለት እዚህ ዌብ ሳይት ላይ አውጥተነዋል።

መቼም ማንም እንደሚያውቀው ቤተ ክርስቲያናችን መመሪያዋ የተመሠረተው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው። ታዲያ እስቲ ከላይ የተፈጠረውን ሁኔታ ከቅዱስ ጴጥሮስ ሁኔታ ጋር እናነጻጽረው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እስከሞትም ቢሆን አልለይህም ሲለው የነበረውን አምላኩን፣ ጌታ በተያዘባት ሌሊት ዶሮ ሳይጮህ 3 ጊዜ ክዶታል (ማር. 14፣66 - 72)። ይሁን እንጂ ጌታ ከተነሳ በኋላ ጴጥሮስን በአለፈው ጊዜ ክደኸኛል፤ ስለዚህ ከአሁን ጊዜ ጀምሮ አልፈልግህም ሂድ ብሎ አላባረረውም። እንዲያውም ጴጥሮስ ሆይ ትወደኛለህ ን? ብሎ ከጠየቀው በኋላ የተሰጠው ኃላፊነት በጎቼን አሰማራ የሚል ነበር (ዮሐ.21፤15-19)።ጌታ ተጸጽተው ለሚመለሱ ፍጹም መሐሪና ይቅር ባይ አምላክ፤ ፍጹም ታጋሽ እንጂ እንደ እኛ በቂምና በበቀል ተነሳስቶ ለመቅጣት የሚቸኩል አምላክ አይደለም። ታዲያ ይህን ላስተዋለ የእነዚህን መምህራኖችን (እንደ ጴጥሮ ስ ክደው ያልነበሩ ነገር ግን በተፈጠሩ ችግሮች ለጊዜው ርቀው የነበሩን) ወይም ተከታይ አባቶችን ስም በ ሐሰት ለማጥፋት ባልተነሳሳ ነበር። እነዚህን መምህራን ባዋረድንና በተሳደብን ቁጥር፤ እነርሱ በረከት የሚ ቀበሉበት፤ እኛ ግን የአጋንንት መሣሪያ መሆናችንን ልናስተውል ይገባል። ስለዚህ አውቀንም ሆነ ሳናውቅ እነዚህን መምህራን ከምእመናን ጋር ለምንለያይ ወይም በወንድማማች መካከል ጠብን፣ መለያየትን ለምን

ፈጥር የእግዚአብሔር በረከት ከእኛ እንደሚርቅና እንዲህ ዓይነቱን ርኩስ ምግባር ነፍሱ አጥብቃ እንደም ትጸየፈው (ምሳሌ 5፤16 -19) ተገንዝበን ከዚህ ዓይነት ምግባር ልንቆጠብ ይገባል።

እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ጠፍቶ የነበረው ልጅ ወደ አባቱ ሲመለስ ምን ዓይነት ደስታ በአባቱ ቤት እንደተፈጠረ ካሰብን፤ ሌሎች ከቤተ ክርስቲያናችን ርቀው የነበሩ ሲመለሱ ልንደሰት ልናቀርባ ቸው እንጂ፤ የበለጠ እንዲርቁና እንዲሸሹ ከሀገር ሀገር እየተከተልን ማሳደድ፤ ስም ለማጥፋት ጉባኤ እያዘጋጀን የሰዎችን አእምሮ መበከል ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሥነ ምግባር ነው።

አንዳንድ የ«ማኅበረ ቅዱሳን» አባላት ትልልቅ የቤተ ክርስቲያንን አባቶችን ከማዋረድ፣ ከማስፈራራት የማይመለሱ፣ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ወይም እንደ አንድ ጥሩ ኢትዮጵያዊ ታላላቆቻቸውን የማያከብሩ፤ ነገር ግን  እነርሱ ራሳቸውን ከማንም በላይ የሚያዩና ስሕተታቸውን መስማት የማይፈልጉ እንደ ዓለማዊ መሪ ከመበቀል የማይመለሱ ናቸው። በቤተ ክርስቲያናችን ካህናት በአገልግሎት ጊዜ የሚቆ ሙበት ረድፍ ወይም ተርታ እንኳ ራሱን የቻለ ሥርዓት አለው። አንድ ዓይነት ሥልጣነ ክህነት (ድቁና) ያ ላቸው ቢሆን እንኳ ቀድሞ የተሾመው ከፍ ብሎ ይቆማል። በቀሳውስት ደረጃም እንዲሁ። በማዕረገ ሲመት ከሁሉም የሚበልጥ እያለ ታች ያለው የተለየ ሥርዓት አይፈጽምም። ምስጢራዊ ሥርዓት የሚፈጸ ምባቸውን ግልጋሎቶች እንኳ ትተን ሌላ ቀላል የሆነ ሊደረግ የማይገባ ምሳሌ ብንሰጥ፤  ከዚህ በፊት በሚ ኒሶታ የቤተ ክርስቲያኑ መሪ ካህን እያሉ ከአዲስ አበባ ከ«ማኅበረ ቅዱሳን» የመጣ አንድ ዲያቆን ኮርስ ተከታትለው ለጨረሱ ልጆች የምስክር ወረቀት መስጠት ምን ያህል ሥርዓት የሌላቸውና ደፋሮች እንደሆኑ ነው። እንዲህ ዓይነት አባቶችን አለማክበርና ማዋረድ ከ«ማኅበረ ቅዱሳን» አባላት የሚታይ ተደጋጋሚ ስ ሕተት ነው።

የሚገርመው «ማኅበረ ቅዱሳን» በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት መምህራን ብቻ አልተወሰነም ነገር ግን ሌሎች በማኅበሩ ቁጥጥር ሥር አንሆንም ያሉትን መሪጌቶችና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን እየተከታተሉ፣ ስሕተት

ለማግኘት የተለያዩ አባላቶቻቸውን መቅርፀ ድምፅ (ቴፕ ሪከርደር) በጉያቸው አስይዘው እየላኩ፤ መምህራኑን በመገፋፋት አንዳንድ ነገሮችን እንዲናገሩ በማድረግ እንዲሁም ደግሞ ያላሉትን እንዲህ ብለው አስተምረዋል አያሉ የሐሰት ምስክር በማቅረብ ከቤተ ክርስቲያን እንዲሰደዱ በማድረግ ለብዙ ዓመታት ቆይተዋል ። እነዚህ  መምህራን በቅኔው፣ በማኅሌቱ፣ በመጻሕፍት ትምህርቱ አልፎም በዘመናዊው ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ናቸው። ታዲያ «ማኅበረ ቅዱሳን» በተለይ እያሳደዳቸው የሚገኘው እነዚህ ዓይነቶቹን መንፈሳዊውንና፣ ሥጋዊውን አጣምረው የሚችሉትን የቤተ ክርስቲያንን ምርጥ ልጆች ነው። በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ በስብከታቸው በጣም የታወቁትን እንደ ዲያቆን በጋሻው ሌሎቹንም አላሠራ በማለት «ማኅበረ ቅዱሳን» ምን ያህል እንቅፋት እንደሆነ ከራሱ ከዲያቆን በጋሻው መስማቱ በቂ ነው። 

በአንጻሩ ደግሞ አብዛኛዎቹ የ«ማኅበረ ቅዱሳን» ዲያቆን ወይም ቄስ ተብለው የሚሾሙት ኪዳን አይደግሙ፣ ቅዳሴ በሥርዓቱ አይቀድሱ፣ ማኅሌት አይቆሙ፣ ቅኔ አይቀኙ ፣ በወጉ እንኳ «አአትብ ገጽዩ.....» ብለው በግእዝ ቋንቋ የዘወትር ጸሎት የማይደግሙ ናቸው። አንዳንዶቹ የዚሁ ማኅበር አባላት የመጡት ምናልባት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለያዩ የአካዳሚክ ትምህርት እንደ ሳይንስ፣ ሕግ ወዘተ ተምረው እንጂ እነሱ እንደሚያሳድዷቸው የቤተ ክርስቲያን መምህራን ከሥነ መለኮት ት/ቤት (ቲዎሎጂ ፋክልቲ) አይደለም። በዓለማዊውም አሠራር ቢሆን ባዮሎጂ ያጠና ሰው የሂሳብ ፕሮፌሰር ወይም ደግሞ ጂኦግራፊ ያጠና የሮኬት ሳይንስ አስተማሪ ሊሆን አይችልም። ታዲያ ከዚያ የመጡት ልጆች እንዴት ሆነው ነው ጥልቅ የሆነውን የቲዎሎጂ ትምህርት እናውቃለን ብለው በድፍረት ለማስተማር የተነሱት አልፎም ደግሞ ከእኛ የበለጠ አዋቂ የለም የሚሉት? አንዳንዶቹ እንደሚሉት አቡነ ጎርጎርዮስ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የ3 ወር ኮርስ በዝዋይ እንደወሰዱ ነው። ከዚያ ውጭ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን ወይም ከሌሎች የተተረጎሙ መጻሕፍትን ትንሽ ከማንበብ በስተቀር የአባቶቻችንን አስተምህሮ ያልሰሙና ያልዳሰሱ ናቸው። ታዲያ እነዚህ ሕጻናት እንዴት ሆነው ነው ለስንት ዓመታት ወይም መላ ሕይወታቸውን በመንፈሳዊ ት/ቤትና አገልግሎት ላይ ካሳለፉት ምምህራን ጋር የሚተካከሉት? በጣም ደግሞ የሚገርመው የዚሁ ማኅበር አባለት በተሰጣቸ

ው ሥልጣነ ክህነት ላይ የሚደረብላቸው የማዕረግ ስም ነው። ስንቶች ሊቃውንት ስንት ዓመታት ሙሉ በቅኔ፣ በዜማ፣ በመጻሕፍት ትምህርት ቤት ተምረው ያገኙትን የማዕረግ ስም በተፈጠረው አጋጣሚ አግኝተው፣ ተሸክመው፤ ራሳቸውን ከማንም በላይ አድርገው፤ ስሕተታቸው ሲነገራቸው ለመስማት ፍላጎቱ የላቸው።

እንግዲህ ከጽሑፉ እንደምንረዳው የ«ማኅበረ ቅዱሳን» አባላት ልክ እንደ ፖለቲካ ድርጅት ከእነርሱ በዕውቀት የሚበልጡትን ከቤተ ክርስቲያን ካባረሩ ብቻ፤ እንደልባቸው በቤተ ክርስቲያኒቷ መድርክ ላይ አለምንም ከልካይና ተቆጪ መፈንጨት እንደሚችሉ ስለገባቸው ይመስላል መምህራንን የማሳደድ ዘመቻ የያዙት።

ስለዚህ በዚህ ዘመን ያለን ክርስቲያኖች የክርስቶስ ወንጌለ መንግሥትን የሚሰብኩትን የቤተ ክርስቲያን መምህራን የምናሳድድ ከሆነ፤ ማንም ቢሆን የወንድሙን በደል አያስብ ብላ ከምታስተምረው ቤተ ክርስቲያን የወጣን ነው ብሎ ለማሰብ አስቸጋሪ ነው። በተጨማሪም በምናደርገው የስም ማጥፋት ዘመቻ ተሰናክለው ለሚቀሩ ተጠያቂዎች ነን፤ ምክኒያቱም ጌታ ራሱ በምድር ላይ ያስተምር በነበረበት ጊዜ «ከእነዚህ ታናናሾችን አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ አስሮ ወደ ጥልቅ ባህር መስጠም ይሻለው ነበር «ማቴ 18፣6-7» የሚለውን ልናስብ ይገባል። በአንጻሩ ደግሞ አንድ ሰው በዳነ ጊዜ በእግዚአብሔርና በመላእክቱ ዘንድ ታላቅ ደስታ ይሆናል የሚለውን አስበን እነዚህ መምህራን በሚሰብኩት ሌላው ቢቀር የአንድ ሰው ነፍስ መትረፉን በማሰብ ከዚህ ክፉ ድርጊት ልንቆጠብ ይገባል። ቃሉን የምንፈጽም እንጂ ሰሚዎች ብቻ መሆን የለብንም (ያዕ. 1፣22)፤ አለበለዚያ ከበረከት ይልቅ እርግማንን በራሳችን ላይ እንሰበስባለን።

ስለዚህ ምዕመናን አንዳንድ ወጣቶች በሚፈጥሩት የስም ማጥፋት እየተደናገራችሁ እናንተም መልሳችሁ ተባባሪ በመሆን የእግዚአብሔር መንግሥት እንዳይስፋፋ እንቅፋት እንዳትሆኑ፤ ከላይ እንደተጠቀሰውም ከእግዚአብሔር ልጅነት እንዳትለዩ ልትጠነቀቁ ይገባል። ሌላው ቢቀር መምህራኑን ዕድል ሰጥተናቸው ልንሰማቸውና በእርግጥ እንደተባለው ከቤተ ክርስቲያናችን ውጭ የሆነ ትምህርት ካስተማሩ እዚው ጠይቆ

መረዳት እንጂ፤ በዚህ የስም ማጥፋት ዘመቻ የሚነገረውን ብቻ ሰምቶ መነዳት አእምሮ እንደሌለን ያስገምታል።

አሁንም «ማኅበረ ቅዱሳን» ሆነ ሌሎች በስም የማጥፋት ዘመቻ የተሰማራን ለእግዚአብሔር መንግሥት መስፋፋት እንቅፋት የሆንን ከአሁን ጀምሮ ከእንደዚህ ዓይነት እግዚአብሔርን ከሚያሳዝን ምግባር ልንቆጠብ ይገባል። ከስም ማጥፋት ይልቅ ለወንጌል መስፋፋት፤ በመክሊታችን ልናተርፍና ከአምላካችን በረከትን ልንቀበል ልንጥር ይገባል። በዘመን የቀደሙ አባቶቻችን ፈለግ በመከተል፤ ትምህርታቸውን በመከተል ፤ ሕይወታቸውን ምሳሌ አድርገን የተውልንን መጻሕፍት በማገላበጥ መማር እንጂ፤ በራሳችን ስሜት ብቻ እየተመራን ይህ ማለት እንደዚህ ማለቱ ነው እያልን ሥርዓቶችን እየፈጠርን መሄድ ቤተ ክርስቲያንን ወደ ከፍተኛ ችግር ላይ የሚጥል ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ሀገራችን እንዲባርክልን በቸርነቱ እንዲጎበኘን፤ አስተዋይ አእምሮን እንዲሰጠንና ለወንጌለ መንግሥት መስፋፋት መሣሪያዎቹ እንድንሆን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁን።

www.ethiopianorthodox.org team!

**ጥር** 2002